## የደብሩ ፍሬ ሃይማኖት ሰንበት ት/ቤት መልዕክት

**"ልጆቼ ኑ ስሙኝ እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራችኋለሁ" መዝ. 33፡11**

ልበ አምላክ ዳዊት በመዝሙሩ እንደተናገረው እግዚአብሔርን መፍራትና የቅድስናን መንገድ ተረድቶ፣ በእምነት ጎልምሶ፣ በመልካም ምግባር እግዚአብሔርን አስደስቶ ለሰማያዊ ተስፋ ለመዘጋጀት እግዚአብሔርን መፍራትን መማር ያስፈልጋል፡፡ እግዚአብሔርን መፍራት ማለት በስጋዊ አስተሳሰብ ምድራዊ ኃይለኞችን ከምንፈራበት የመገደድ ፍርሃት በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ እግዚአብሔርን የምንፈራው መልካምና ታዛዥ ልጅ የሚራራለት አባቱን እንደሚፈራው ዓይነት የፍቅር ፍርሃት ነው፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ ወንጌላዊ እንዳለ "ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጅ በፍቅር ፍርሃት የለም" 1ኛ. ዮሐ. 4፡18፡፡ በፍጹም ፍቅር እግዚአብሔርን ለመፍራት፣ እግዚአብሔርን ለመውደድ፣ ይህንንም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳስተማረን ትዕዛዛቱን በመጠበቅ ለመግለጽ እግዚአብሔርን ማወቅ፣ የቅዱሳት መጻህፍትን ምስጢርና ትርጓሜ መረዳት፣ በየዘመኑ የሚመጡ የሐሰት ትምህርቶችንና፣ የሐሰት ተዓምራትን ከእውነተኛው የቤተክርስቲያን ድምጽ በመለየት ራስን በመንፈሳዊ አለት መሰረትነት ማነጽ ያስፈልጋል፡፡

በተለይም ደግሞ አስመሳይነት፣ ዘረኝነት፣ አድመኝነት፣ በቤተክርስቲያን ጉዳይ ከቤተክርስቲያን እውነተኛ ድምጽ ይልቅ የግለሰቦችና የቡድኖች በእልህ የተሞላና እውቀትና መንፈሳዊነት የተለየው ሽኩቻ በበዛበት በዚህ ዘመን ይህንን አብዝተን ልንፈጽም ያስፈልጋል፡፡ ይህ ዘመን የኢ-አማንያኑን፣ በግልጽ ከቤተክርስቲያን አንድነት የተለዩትን መናፍቃን፣ በቤተክርስቲያን ጉያ ተቀምጠው የቤተክርስቲያንን እውነተኛ ትምህርት ለመበረዝና ለማጥፋት የሚማስኑትን ውሉደ-ከለባት እንዲሁም በገንዘብ፣ በዝናና በዘረኝነት መረብ ተታልለው በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በቤተክርስቲያን ላይ በጠላትነት የተነሱባትን ሰዎች በየደረስንበት ተቋቁመን አንዲት፣ ቅድስት፣ ሐዋርያዊትና ኩላዊት የሆነች የቤተክርስቲያናችንን ልዕልና በሁሉም መስክ ለማስከበር የምንሯሯጥበት መሆን አለበት፡፡

ይህን መንፈሳዊ ተጋድሎ መፈጸም ለቤተክርስቲያን መደበኛ ካህናት ብቻ የሚተው ኃላፊነት አይደለም፡፡ ሁላችንም በየመስኩ የሚገባንን ካላደረግን በሩቅ የምንሰማው መለያየት፣ ክፍፍልና በክፉ ልምምድ ህገ-እግዚአብሔርንና ስርዓተ ቤተክርስቲያንን ማጥፋት በቅርብ ሲደረግ ብናየው ልንደነቅ አይገባም፡፡ ለዚህም ነው ሰንበት ት/ቤታችን ከዓላማዎቹ መካከል የቤተክርስቲያንን ሐዋርያዊ አስተምህሮ ለምዕመናን ማሳወቅንና ሕፃናትና ወጣቶችን በመንፈሳዊ እውቀትና ምግባር ማነጽን ቅድሚያ የሰጠው፡፡ ይህ ዓላማ በሂደት የምንፈጽመውና የሁሉንም የአጥቢያችን ምዕመናን ተሳትፎና መረዳት የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህም እንዲረዳን ሰንበት ት/ቤታችን ሳምንታዊ መርሃ ግብር አዘጋጅቶ በየሳምንቱ ቅዳሜ ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ 2 ሰዓት (From 6:00 to 8:00 PM) ትምህርተ ወንጌልን በስብከትና በተከታታይ ትምህርት መልኩ እያቀረበ ይገኛል፡፡ ምዕመናን ያልተበረዘ የቃለ እግዚአብሔር እውቀት እንዲኖራቸው የቤተክርስቲያንን አስተዳደራዊ መዋቅር በጠበቀ መልኩ የሚሰጡ ትምህርቶችን በሚገባ መከታተል ያስፈልጋል፡፡

ለሀገራችን ለኢትዮጵያ የምስራች የተባለ የክርስቶስን ወንጌል የሰበከ ሐዋርያው ቅዱስ ፊልጶስ የኢትዮጵያዊቷ ንግስት ሕንደኬ አዛዥና ጃንደረባ የነበረውን ባኮስን "በእውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?" ባለው ጊዜ በመንፈሳዊ ትህትና የተሞላው ባኮስ የመለሰለት መልስ ለሁላችንም አርዓያ የሚሆን ነው፡፡ "እርሱም የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት ይቻለኛል? አለው" ሐዋ. 8፡30 እኛም የባኮስን አርዓያነት ተከትለን በቤተክርስቲያናችን አባቶች የሚሰጠንን ትምህርት ለመከተል

የሰንበት ት/ቤት ጉባኤን ያለመሰልቸት መከታተልና እንደአቅማችንና ፍላጎታችን መሳተፍ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህም የቤተክርስቲያናችን አገልጋዮች የአቅማቸውን እየተወጡ ይገኛሉ፡፡ ወደፊትም ክፍተቶችን በመሙላት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንጥራለን፡፡ በመሆኑም በአጥቢያችን የምትገኙ ምዕመናን፣ በተለይም ወጣቶች የጉባኤያችን ተሳታፊ በመሆን ክርስቲያናዊ ኃላፊነታችንን እንድንወጣ፣ ለላቀ መንፈሳዊ ተጋድሎ እንድንነቃቃ በስሙ በተሰበሰብንበት በሊቀ መላዕክት በቅዱስ ሚካኤል ስም እንማጸናችኋለን፡፡

ቅን በሆነ መንፈሳዊ አገልግሎት እንደ ሰንበት ት/ቤታችን ስያሜ መልካም የሆነ ፍሬ-ሃይማኖትን እንድናፈራ የቅዱሳን አምላክ፣ የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ይርዳን፡፡